# ለመበደል፤ ለመበደል...

(ነቅዓ ጥበብ፣ ከለንደን)

እሱ ያመጣውን፣ እሱ እስኪመልሰው፣
ይቅር በለን ማለት፣ አያንሰውም ለሰው፤
«ለመበደል እማ፣ ወታደር በድሏል፣
ታዲያ ምን ይደረግ፣ ባላገር ይክሳል።»
እንደሚሉት ሁሉ፣ አባቶች ሲጠቅሱ፣
ዛሬም ያው ሆነና፣ ያልበደሉ ካሱ።

«አለባብሰው ቢያርሱ፣
ባረም ይመለሱ።
አዳም በበደለ፣ መዲኃኔዓለም ክሶ፣
ቀራኒዮ ቆሞ፣ ከለሜዳ ለብሶ።»
ነገሩ እንደዚያ ነው፣ ዞሮ ተመልሶ፣
እውነት ሲጎመዝዝ፣ ይመራል ከኮሶ።
ከተወጠረበት ዓለም አቀፍ እስር፣
ወያኔ እንድፈታ፣ በይቅርታ ምስጢር፣
ሽማግሎች ጣሩ፣ ውጤቱ እንዲሰምር፣
ሽምግሌ አይጥፉ፣ በቀዬ በሀገር፣
እርግጥ ነው ደስ ይላል፣ ይቅርታ ሲበሰር፣
ግን እኮ ጉዳዩ፣ በደንብ ሲመረመር፣
እነመለስ ናቸው የተፈቱት ከእስር።

የይቅርታ ጌቶች፣ እንኳን ድስ ያላችሁ፣
ያገር ሽምግሎች፣ ከእስር ፈቷችሁ።
ኢሕአዴግን ይቅናው፣ ላረገው ወሮታ፣
ሰንሰለቱ ይውለቅ፣ ላንደኛው ይፈታ፣
እንኳን ደስ አላችሁ፣
እንኳን ደስ አለን፣
እንታገላለን እየተያዩን፣
እንኳን ከጨለማው አላቀቀልን፣
የመሰፍን ጥናቱ፣ ምድረ - ኢትዮጵያ፣
የሁሉም መገኛ፣ ታላቋ ገበያ፣
ምንጊዜም ኑሪልን፣ በነኃይሉ አርአያ፣
ቀንም ሆነ ሌሊት፣ ብሶት ስናወጋ፣
ይኸው ወገግ አለ፣ ብርሃኑ ነጋ፣
ጠጋ፣ ጠጋ፣ ጠጋ፣
ሁሉም ጠጋ፣ ጠጋ፣
ምንጊዜም ኃይል ነው፣ የአንድነት ፀጋ፣
በቃል ኪዳን ማተብ፣ በትግል ፍካሬ፣
በቅንጅት መንፈስ፣ በብርቱካን ፍሬ፣
እንደገና ኩሪ፣ ውዲቷ ሀገሬ፣
ከዚህ ያደረሰን፣
እግዚአብሄር ይመስገን።

(July 21, 2007)